*መስከረም 24 ቀን 1998 ዓ.ም.*

ለአቶ ጌታቸው ጎንፋ
በፍትሕ ሚኒስቴር የማኅበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ
<u>አዲስ አበባ</u>

መስከረም 6 ቀን 1998 ዓ.ም በቁጥር 11/275/ሠ 134 ከፍትሕ ሚኒስቴር የማኅበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ለክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት (ሲ.አር.ዲ.ኤ) የተጻፈው ደብዳቤ ደርሶናል።

ከደብዳቤው እንደተረዳነው እ.ኤ.አ. ጁን 20 ቀን 2005 በወቅቱ የነበረው የሲ.አር.ዲ.ኤ. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባወጣው የአቋም መግለጫ ምክንያት የኮሚቴው ተግባር እንደ ሕገወጥ እንዲፈረጅ ወይም እንዲቆጠር መደረጉ በእጅጉ አስደንግጦናል፣ አሳዝኖናልም።

ሲ.አር.ዲ.ኤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕግን መሠረት አድርጎ፣ በሕግ ጠለላና እገዛ ሥር ሆኖ በምግባረ ሰናይና በልማት ተግባራት ተሰማርቶ ከ30 ዓመታት በላይ ሲሠራ የቆየና፣ አሁንም በዚሁ መሠረት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው። ሲ.አር.ዲ.ኤ. ከተቋቋመለት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በተፈጥሮና ሰው-ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ ወገኖችን ችግር ማቃለልና መቅረፍ መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም ተግባር ሊያግዙ የሚችሉ የአድቮከሲ ሥራዎችን (የአቋም መግለጫዎች ማውጣትን ጨምሮ) ሲያከናውን ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም። መጋቢት 22 ቀን 1990 ዓ.ም. ከፍትህ ሚኒስቴር የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት የፈቃድ እድሳት ካገኘ በኋላ እንኳን ለስምንት ዓመታት የአድቮከሲ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ሲ.አር.ዲ.ኤ. የነዚህን ተግባራት ክንውንና አልፎ አልፎ መሻሻል ስለተደረገባቸው የመመሥረቻ ጽሁፎችና የመተዳደሪያ ደንቦች የሚገልጹ ሪፖርቶቹን ለማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት በየዓመቱ ሲያቀርብ ቆይቷል። የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤቱም አመታዊ ሪፖርቶቹን ያለምንም ተቃውሞ ተቀብሎ የድርጅቱን የሥራ ፈቃድ ሲያድስ ቆይቷል።

ከዚህም በላይ በሲ.አር.ዲ.ኤ ስትራቴጂክ እቅድ ውይይት ሂደት ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥታዊ ድርጅት ተወካዮች (በወቅቱ የነበሩትን የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤቱን ኃላፊ ጨምሮ) የተሳተፉ ሲሆን፣ የሲ.አር.ዲ.ኤን የአድቮከሲ ሥራዎች በሰፊው የሚተነትነውና በመጨረሻም የፀደቀው የእቅድ ሰነድ እ.ኤ.አ. በጁን 19 ቀን 1998 በወቅቱ የፍትህ ሚኒስትር ለነበሩት ስለተላከ ሰነዱ በሚኒስቴሩ መ/ቤት ይገኛል። የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት መጋቢት 22 ቀን 1990 ዓ.ም. ለሲ.አር.ዲ.ኤ የሰጠውን የፈቃድ መግለጫና የሁኔታዎች ሰነድ እንኳን ብንወስድ፣ በአንቀጽ 1 (ሐ) መሠረት ሲ.አር.ዲ.ኤ ከተፈቀዱለት ተግባራት መሀከል አንዱ የማህበሩን አባላት የጋራ አቋምና ፖሊሲዎች ማውጣትን ያካተተ ነው። በመሆኑም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የማህበሩ አባላትን ወክሎ እንዲሠራ በተሰጠው ስልጣን (mandate) መሠረት በአገር ደረጃ አሳሳቢ በሆነው በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ ሲያወጣ ተገቢና በሕግ የተፈቀደለት ሥራ መሆኑን በማመን ነው።

.../2

*መስከረም 24 ቀን 1998 ዓ.ም.*

ለአቶ ጌታቸው ጎንፋ
በፍትሕ ሚኒስቴር የማኅበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ
<u>አዲስ አበባ</u>

ምናልባትም ይህ መግለጫ የተሰጠበት ዓላማና መንፈስ በወቅቱ አገራችን ከነበረችበት ያለመረጋጋት ሁኔታ ጋር ሲገናዘብ በአሉታዊ ጎኑ ታይቶ ካልሆነ በስተቀር፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መግለጫውን ሲያወጣ በወቅቱ የነበረውን ውጥረት ለማርገብ ይረዳል ከሚል ቅን ልቡና እና ከዜግነት ኃላፊነት በመነሳት፣ እንዲሁም ሲ.አር.ዲ.ኤ. እንደ ሲቪል ማኅበረሰብ አባልነቱ የሚጠበቅበትን ተግባር በሥራ ላይ እንዳዋለ በማመን ነው:: በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ በተረጋገጠው መብትና በሀገሪቱ በመገንባት ላይ ባለው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በመበረታታት ነው::

ስለዚህ የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤቱ ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጥ ሁኔታዎች አገናዝቦና በገንቢና በጎ መልኩ አይቶ ለድርጅቱ የሰጠውን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲያነሳልን አሁን በሥራ ላይ ያለው የሲ.አር.ዲ.ኤ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በአባል ድርጅቶቹ ስም በትህትና ይጠይቃል::

ይህ ልዩ ሁኔታ ያስከተለው አለመግባባት ወይም በጎ ያልሆነ አመለካከት ተስተካክሎ ከማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤቱ ጋር ያለው መልካም እና ቀና የሥራ ትብብርና ግንኙነት እንደሚቀጥል ተስፋ በማድረግ፣ ሲ.አር.ዲ.ኤ. ከተመሠረተ ጀምሮ ያለምንም እንከን ሕጋዊ ሆኖ የቆየና ወደፊትም ሕጋዊ በሆነ መንገድ ብቻ የሚንቀሳቀስ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልናረጋግጥ እንወዳለን::

ከሰላምታ ጋር

ገብርኤል ጋላቲስ
የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ (ቦርድ) ሰብሳቢ

ግልባጭ: - ለሚኒስትሩ ጽ/ቤት
- ለሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት
ፍትሕ ሚኒስቴር
- ለመገናኛ ብዙኃን
<u>አዲስ አበባ</u>